# የኤርትራ የመገንጠል መዘዝና ከኢትዮጵያ ጋር የቀዶ ጥገና ግንኙነት

ለኣከ ገብረፃድቕ
መስከረም 2፡ 2002 ዓ ም

<u>ክፍል ሁለት</u>

## 2. የኢትዮጵያና ኤርትራ የቀዶ ጥገና ግኑኝነት

በቅድሚያ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን፣ ለፕሮፌሰር ዳንኤልና ተስፋፅዮን ጭምር እንኳን ለኣዲሱ ዓመት በዓል ኣደረሳቹህ እላለሁ።

በክፍል ኣንድ ባቀረብኩት ፅሁፍ ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ በሚያራምዱት የብሂረሰብ ሽኩቻ ፖለቲካ ያለኝን ተቃውሞና ኣስተያየት ላይ ያተኮረ ነበር።

ገለባዉን ካንጓለልን ዘንድ ወደ ንጥረነገሩ፣ የኢትዮጵያና ኤርትራ ግኑኝነት ጉዳይ ልግባና በተለይ በዚህ ርእስ ያለኝ ዓላማ ሁለቱ ምሁራን ባቀረቡት ተግባራዊነት ባላቸው የኮንፌደሬሽንና ፌደሬሽን ሓሳቦች ላይ የራሴን ኣስተያየት ለመጨመር ነው። እግረ መንገዴም ያቀረቡትን ኣስተያየቶች መነሻ በማድረግ ኣማራጮቹ ባላቸው ልዩነት መሠረት ኣንዱ ከሌላው እንዴት እንደሚበጅ የራሴን ሓሳብ ኣክልበታለሁ።

## በኤርትራ ለጤናማ ግኑኝነት እንቅፋት የሆኑ ማህበረ-ፖለቲካዊ ቀውሶች

ከሁሉም በፊት መጠየቅ ያለበት ጥያቄ እንግዲህ "ያ ሁሉ ጦርነት ኣልፎ ኤርትራ በጥላቻ ምሬት ከኢትዮጵያ ከተለየች በኋላ ኮንፌደሬሽን ወይም ፌደሬሽን ኣሁን ወይም ነገ ለምን ያስፈልጋል?" የሚል ነው። ያለፈውን ስህተት ሙሉ በሙሉ ለማረም ወይስ በትግርኛ "ሥራ የፈታች መኖክሴ ቆብዋን ቀዳ ትሰፋለች" እንደሚባለው የግንጠላው መሠረታዊ ጉድለቶችን የማስተካከያ ሙከራ ነው? ከኣጥሩ ወድያና ወዲህ ሆነው ለሚሟጐቱ ሰዎች ለዚህ የሚሰጡት መልስ እንደ ፖለቲካዊ ኣመለካከታቸውና ግባቸው ሊለያይ ይችላል።

በኔ ኣመለካከት የኢትዮጵያ ሕዝብ የውህደቱን ሓሳብ ለማጤን በእርግጠኛነት ማወቅ የሚፈልገው ኣንድ ትልቅ ቁምነገር ያለ ይመስለኛል፤ ይኸውም የኤርትራ ሕዝብ መገንጠሉ ከጥቅሙ ጉዳቱን ኣመዛዝኖ፣ በተለይም ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ኣመለካከቱን ኣስተካክሎ፣ በኢትዮጵያ የነበረውና ያለው ታሪካዊ ስፍራ ተገንዝቦ ከኢትዮጵያ ወገኑ ጋር በመዋሃድ ለኣገር ብልፅግና የበኩሉን ኣስተዋፅኦ በማድረግ የውጤቱንም ተካፋይ መሆን እንደሚፈልግ ማረጋገጥ ነው።

በተስፋፅዮን መድሃንየ ቀናነት ምንም ጥርጣሬ የለኝም፣ ነገር ግን በኣንፃሩ ደግሞ ተፈላጊ ያልሆነና መወገድ ያለበት ነገር ከኤርትራ ወገን ሆነው ለሚሟጐቱ ሌሎች ኣካላት ዋናውና ዘላቂ ግባቸው በኮንፌደሬሽን ኣመካኝነት ኢትዮጵያን የጎደለውን

የሚያሚሉባት የባእድ ኣገር ለመጠቀም የሚያልሙት ዘዴ መፍጠር ጥረት እንዳለ ነው።

ማንም ሊክደው የማይችልና ለኣንደ ኣፍታም መረሳት የሌለበት፣ በተለይም ኣንድኣንድ የመሓል ኣገር ፖለቲከኞች የማይገነዘቡትና፣ ኤርትራውያን ራሳቸውም የማያምኑት ሓቅ ኤርትራን ለመገንጠል ያበቃ የህብረተሰቡ የስነልቦና፣ ፖለቲካዊ ኣመለካከት፣ የማንነትና፣ የታሪክ ብረዛ ቀውስ ችግሮች ነው። እነዚህ ችግሮች በግኑኝነት እደሳ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ይኖራቸዋል። ችግሮቹ እንደሌሉ ወይም ተራ እንደሆኑ መመልከት የግኑኝነቱ ዓላማ ብልሹ ያደርገዋል።

በነፃነቱ የጥላቻ ንቅናቄ ተኮስኩሶ ያደገው "የኢሳያስ ትውልድ" ቊጥሩ ቀላል ባይሆንም ይህ ንኡስ ከበርቴ እንደ ዋነኛ የኤርትራ ሕዝብ ወኪል በመጠቀም ድምዳሚ ላይ መድረስ ያስቸግራል። ይሁን እንጂ ለፖለቲካው መዋቅርና ሂደት ቅርበት ያለው የከተማ ነዋሪው ከበርቴ የፖለቲካውን ኣቅጣጫ የመወሰን ሓይል ያለው በመሆኑ መናቁም ያስቸግራል። ይህ ትውልድ በጣም ኣደገኛ፣ ጤናማ ያልሆነ የፖለቲካ ኣስተሳሰብና የተዛባ ስነልቦና ያለው ማለትም ትዕቢት፣ ንቀት፣ ፀበኝነት፣ ስድብ፣ ወዘተ በተለይም ከባድ ጥላቻን የመሰለ ክፉ ባህሪ የሚጨምር መጥፎ የትምክህት ኣመሎች (prejudice) የተወጠረ የሕብረተሰብ ክፍል ነው።

ችግሮቹ ቁጥሩ ቀላል ባልሆነ ኤርትራዊ ላይ የሚከሰቱ ስለሆነ ማህበራዊ መዋቅር ያለው ነው ማለት ያስደፍራል። በእርግጥ የሻዕብያና ጀብሃ የነፃነት እንቅስቃሴ ማህበረሰባዊ ኣስተሳሰብን፣ ታሪክንና፣ ማንነትን እንደ ኣዲስ የማነፅ እንቅስቃሴ እንደነበር ይታወቃል። በዚህም ሳብያ ችግሩ ከምሁሩና ፖለቲካ ከበርቴዎች እስከ ተራ ኣላፊ ኣግዳሚው ሰው ድረስ ያንሰራራ ችግር ነው። ኤርትራ ያለችበትም ይሁን ለወደፊቱ ያላት የመነመነ ራስዋን የምትችልበት ዕድልም በትክክል የሚገነዘቡ ኣይመስለኝም። የኢሳያስ ኣፈወርቂ የተሳሳተ መርህና ኣምባገነናዊ ኣስተዳደር በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር የዘለቀ የግጭት ግኑኝነት ብቻ ለሁሉም የኤርትራ ችግሮች እንደ ዋና ሰበብ ማመካኛ ይጠቀሙበታል። ከኢሳያስ ዘመነ ሥልጣን ህልፈት በኋላም ከሚጋርዳቸው የኢትዮጵያና ሕዝብዋ ለዘመናት ለትውልድ ጭምር በመተላለፍ ላይ ያለ ጥላቻ ተላቀው እውነታዉን መረዳት የሚችሉ ኣይመስሉም፤ ብያንስ ብዙ ጊዜ ይፈጃል።

ሻዕብያ በ1990ው የድንበር ጦርነት ከዛም በፊት በኢትዮጵያ በተለይም በጎረቤት የትግራይ ሕዝብ ላይ ጥላቻን በማስረፅ ድል ተቀዳጅቶኣል፤ የሻዕብያ ተራ ወታደር በጦርነቱ ወቅት በሰላማዊ ሕዝብ የፈፀመው ጭካኔ የተሞላው ግፍና ቤተክርስትያናት ላይ ያካሄደው ኣረመንያዊ ውድመት በቀላሉ የሚታለፍ ኣይደለም። በወደመችው ዛላንበሳ ግድግዳዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ገና ያላጠናቀቁ የሻዕብያ ለጋ ወታደሮች የተፃፉት ይህን ከባድ ጥላቻ የሚያንፀባርቁ ብልሹ ኣስተሳሰቦች ራሴ በምስክርነት ኣይቻሎህ። ካለው የተሻለ ውጤት በተኣምር የምንጠብቅ ከሆነ እንግዲህ እስከ ኣሁን ያለው ፖለቲካዊ ግኑኝነት የተቀረፀው ራሳችንና ሌሎችን እንዴት እንደምንመለከት ላይ የተመሠረተ ነው።

የነፃነቱ ጦርነት ለማሳካት ከፍተኛ የማንነትና የታሪክ ክሕደት ዘመቻ የተካሄደበት ይህ ህብረተሰብ፣ የማጥራት ሌላ ዘመቻ እንደሚያስፈልግ ያህል ከባድ ነው። እነዚህ ችግሮች ከጎረቤቱና ኣምሳያው ከሆነው ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚያውቀውና መጥፎ ተመክሮ ያለው ኣይኖርም። የጠቀስኩዋቸው የትምክህትና የጥላቻ ባህሪዎች በኤርትራ ህብረተሰብም መሓከል ጎጥና ኣውራጃን በመለያየት በሰፊው የሚታዩ ችግሮች ስለ ሆኑ መጨረሻው ምን ላይ ነው ብሎ ብዙም ማሰብ ኣያስፈልግም።

የኢሳያስ ትውልድ የተጠናወተው የኣልበገሬነት ስነልቦናና ያን ዓይነት የኣስተሳሰብ ቀውስ የሚያስከትለው ውድቀት ራሱን-በራሱ ለማረም ያህል የ1990ው ዓይነት ጦርነት የሚያስፈልግ ኣይመስለኝም። በእርግጥ ያ ጦርነት ኣልበገሬነትና ትዕቢት ማስተንፈስ ከቻለ በኤርትራውያን የሚፈለገው ኣዎንታዊ የኣስተሳሰብ ለውጥ በማስመዝገብ ወደ ውህደቱ ያቀና ትልቅ እርምጃ ነው ማለት ነው። ይህ ዓይነት የኣስተሳሰብና ስነልቦና ችግር ባለበት ሁኔታ ግን ስለ ምንነጋገርበት ጉዳይ ርቱዕ በሆነ መንገድ የሚያዋጣ መንገድ በማሰላሰል ጥሩ ውሳኔ ላይ መድረስ ያስቸግራል።

እንግዲህ በነዚህ ቀውሶች ኣምሳያ የተቀረፀው የኤርትራ ፖለቲካዊ ህልውና የኢትዮጵያን ፖለቲከዊ እርጋታ እንዴት እያደፈረሰው እንደሚገኝ እንመልከት። የኢሳያስ ኣመራር በኢትዮጵያ እጅ ማስገባት ብቻ ሳይወሰን ሌሎች ተራ ኤርትራውያንም በኢትዮጵያ ወቅታዊ ኣሉታዊ ፖለቲካ ላይ በጣም የተዘፈቁ ናቸው። እንግዲህ ኤርትራ ከነፃነቱ በፊትም በኋላም በኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ጣልቃ በመግባት የማናጋቱን ተግባር እንደቀጠለችበት ነው። የኤርትራ የጣልቃ ገብነት ፖለቲካም በኢትዮጵያ ያሉ ኣንድኣንድ የፖለቲካና ምሁር ከበርቴዎች ኣመለካከት በመቅረፅ ላይ ስር የሰደደ ችላ የማይባል ሚና ኣለው። ሻዕብያ ገና ከጥዋቱ በሞያ የሰለጠነበት በህወሓት ላይ እንዳደረገው በውክልና የሚሰሩለት ምልምል ቅጥረኞች ኣሁን ባሉት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶችም ይጠቀምበታል። ከመሓል ኣገር ተንደርድረው "ካለኔ ማን ኣዋቂ ኣለ"፣ ኢትዮጵያን "ከወያኔ" ነፃ እናወጣለን፣ ወዘተርፈ በማለት በሥልጣን ያለው መንግሥት ዓይነት ለወደፊቱ ስፍራ እንዳይኖረው መፍትሄ ላይ ከማትኮር ይልቅ በትግራይ ብሄረሰብ ጥላች ምክንያት በድብቅ ኣጀንዳ ተነሳስተው ኣገሪቱን ወደ ባሰ ኣዘቅጥ ለመጣል የኢሳያስን ሞግዚትነት የወሰዱ መብዛታቸው የሚታወቅ ነው። የኤርትራን ኣዲስ ግኑኝነት የሚናፍቁ ሰዎችም ቢሆኑ ገና ብዙ መማር የሚገባቸው ነገር ስላለ ሌላውን ነፃ ማውጣት ይቅርና መጀመርያ ራሳቸውን ነፃ ማውጣት ይኖርባቸዋል። ምናልባት እነሱን ነፃ ለማውጣት የሌላውን ጥረት የሚያስፈልግበት ሁኔታም ይኖራል።

እዚህ ላይ ችላ ተብሎ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ዳንኤል ክንዴ የሚሹት የኤርትራን ፈደሬሽን ግኑኝነት በትግራይ ላይ ያላቸው ቅሬታ ይሁን ጥላቻ ምክንያት በተፃራሪነት ለመቋቋም የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ዘዴ እንደሆነ ነው የምገነዘበው። በትግራይና ኤርትራ ያለ ቅራኔ በደንብ ስለሚያውቁ የቂም በቀል መወጣጫ ሊጠቀሙበት ሙከራ እንደሚያደርጉም ከፅሁፋቸው መረዳት ይቻላል። በኤርትራ ግኑኝነት ላይ በመሞርኮስ መድረኩን ስለ ፀረ-ትግራይ ያላቸው ኣቋም ለፈፉ በሰፊው ተጠቅመውበታል። ብዙ የመሓል ኣገር ንኡስከበርቴዎች ትግራይን ነጥሎ ዒላማ በማድረግ ይህን ቅራኔ ለጥቅማቸው ሊጠቀሙበት ላይ ታች ሲሉ ይታያሉ። ይህ ዓይነቱ ኣስተሳሰብ ግንቦት 7 ከሚጠቀምበት የትግራይ ህብረተሰብ

የጥላቻ ዘመቻ ውጤት ጋር ልዩነት የለውም። ውጤቱም ያማረ አይሆንም፤ በዚህ መንገድ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ማህበረሰብ ለመቀላቀልስ ይቅርና፣ ትግራይን ወደ ደርጉ ዓይነት ኤርትራ ያስገነጠለበት ድንፋታና ንረት የሚፈጥር አደገኛና የብሄረሰቦች ግጭት የሚቀሰቅስ ወንጀለኛ አካሄድ የሚያመራ በመሆኑ ግድ ያለው ኢትዮጵያዊ ይህን የመግታት ሌላ ከባድ ሥራ ይጠብቀዋል። ኤርትራ የተገነጠለችው በሻዕብያ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ችሎታ ሳይሆን በአብዛኛው የኤርትራን ሕዝብ ጨርሶ ያገለለ የደርግ የደንቆሮዎች ጦርነትና በወያነ መሪዎች የክሕደት ወንጀል መሆኑ ማስታወስ ይኖርብናል። ስለዚህ የሚፈለገው የኮንፌደሬሽን ወይም የፌደሬሽን ግኑኝነት እስካሁን ባነሳሁዋቸው ማህበራ-ፖለቲካዊ ቀውሶች ምክንያት በፅኑ መንፈስ ላይ የተመሠረተ አለ መሆኑ ማሳየት ሞክሬአለሁ።

ወደ ተስፋፅዮን መድሃንየና ዳንኤል ክንዴ የኢትዮጵያና ኤርትራ ግኑኝነት ችግር መፍትሂ አቋም ተመልሰን ስንመለከት ተስፋፅዮን መድሃንየ ኢትዮጵያና ኤርትራ የሂዱበትን አስከፊ ታሪክና በኤርትራ ህብረተሰብ ያለውን ስጋትና አለመተማመን በመገንዘብ የፌደሬሽኑ ሂደት በጥንቃቄ ይቀርቡታል። በፌደሬሽን ለማዋሃድ እንድያዉም ኣንድ እርምጃ ወደ ኋላ ራቅ ብሎ በኮንፌደሬሽን መጀመር ኣለበት ባይ ናቸው። በእርግጥ የእርስ በእርስ ጦርነቱ ወቅት "በ80ዎቹ" (ገፅ ፩ ላይ እንደጠቀሱት) ከነበራቸው የፌደሬሽን ኣስፈላጊነት አቋም በጣም ርቀው ወደ ኋለ እንዳፈገፈጉ ኣውስተዋል።

ተስፋፅዮን፣ ኤርትራ ከደርጊቱ ኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን እንድትቆይ በነበራቸው ፍላጎት ቢጥሩም፣ የኤርትራ ተቃዋሚ ሓይሎችና ሕዝብ የጋለው ጦርነት ያረገዘው የነፃነት ማና ገና በማዋለድ ላይ በነበሩበት ወቅት የከረረ የነፃነት አቋም የሚከተሉና የጦርነቱ ፍፃሜ ውጤት ሲንጋፖራዊት ወይም ኢስራኤላዊት-ኤርትራ ለማየት የሚጓጉ እንጂ ስለ ፌደሬሽን ማቅማማት የማይታሰብ ሁኔታ ነበር። ትግሉ ራሱ ከኢትዮጵያ ጋር ሁሉም ዓይነት በጎ ግኑኝነትን የሚፃረር ዓላማ ነበረው። በኣንድ ወቅት በእርግጥ ሻዕብያ ከኢትዮጵያ ጋር አዲስ ግኑኝነት ለመንደፍ ኣቅማምቶ እንደነበረ ቢታወቅም በደረሰበት ወታደራዊ ኪሳራ ሳብያ ነበር። የደርግ ፋሽስታዊ ስርዓትም ባህሪው ከሚፈቅድለት ውጭ የሆነ የፌደሬሽን ስርዐት ምስረታ የሚፈቅድ ኣልነበረም። ኣሁን ያለንበት ጊዜ ይልቅ የኤርትራ ሕዝብ "የነፃነቱን" እጅግ መራራ ፍሬ የቀመሰበት፣ በጦርነት ግፌት በስሜት የሚነዳበት ጊዜ ኣልፎ ረጋ ብሎ ራሱን በሁለት እጆቹ ኣስደግፎ ኣስከፊውን ንሮ ቁልቁል በሚመለከትበት ሁኔታ፣ ከኢትዮጵያ ጋር የፌደሬሽን ውሕደት ጠቀሜታ በጥሞና ኣውርዶና ኣውጥቶ በማሰላሰል ለዚህም እዉንነት የሚጠይቅበት ኣመቺ ጊዜ የተፈጠረ ይመስለኛል። ከኣሁን በኋላ የሚደረግ ግኑኝነት ያለፈውን ውድመትና ስህተት የሚታረምበት እንጂ ኤርትራን በልዩ ሁኔታ የምትስታመምበት ጥረት መሆን የለበትም።

ቅድም እንደጠቀስኩት ጥርጣሬንና ስጋትን የሚያበራክቱ የኤርትራውያን የጥላቻ፣ የማንነትና፣ የታሪክ ክህደቶች መወገድ ይኖርባቸዋል። ኤርትራውያንም ያላቸውን ስጋት ለማርገብ ሕዝብ የሚያምንበት ዲሞክራስያዊ ስርዓት በተለይ በኣስተናጋጅዋ ኢትዮጵያ መመሥረት ይኖርበታል። ከተገቢው ስርዓት ምሥረታ ውጭ ሌላ ኣስተማማኝ መፍትሂ የሚሰጥ ግኑኝነት ኣይኖርም። ኮንፌደሬሽንም ኣንዱ ሊሆን ኣይችልም። በኢትዮጵያ ሁሉንም ብሄረሰቦች/ክፍለሃገሮች በፌደሬሽን የሚያዋቅር

ዲሞክራስያዊ ስርዓት ካለ ኤርትራውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በኣብላጫ የሚጠይቁት ወይም የሚያገኙት መብት ሊኖር ኣይችልም ወይም መኖር የለበትም። ኤርትራውያን የሚኖራቸው ዋስትናም ሌሎች ኢትዮጵያውያን የሚያምኑበት የዚሁ የዲሞክራስያዊ ስርዓት ምሥረታ ዋስትና ነው። እዚህ ላይ በኣፅንኦት ማሳየት የምፈልገው (ኮንፌደሬሽን የሚባል ነገር የማይታሰብ ሲሆን) የፌደሬሽን ውህደት እንዲሳካ ግን ጥያቄው ከኢትዮጵያ ሳይሆን በቅድምያ ከኤርትራውያን የፈለቀ ቅኑ ፍላጎት መሆን እንዳለበት ነው። ለዚህም ሁለቱም ኣገሮች የሚኖራቸው ከፍተኛ የጥቅም ልዩነት ኣኳያ በርካታ ምክንያቶች መዘርዘር ወደ ኋላ እመጣበታለሁ።

ሁለቱም ምሁራን በኮንፌደሬሽንና ፌደሬሽን ኣማራጮች በወሰዱት ኣቋም፣ በሁለቱም ኣገሮች የዲሞክራስያዊ ሥርዓት ለውጥ ኣስፈላጊነት ገልፀዋል። የዲሞክራስያዊ ሥርዓት በቅርብ እውን የሚሆንበት ሁኔታና ጊዜ ከኤርትራ ይልቅ በኢትዮጵያ እንደሚሆን በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል። (ይህ እንግዲህ ባለው መንግሥትና ኣገሪቱን ለመበታተን እኩል ኣስተዋፅኦ ከሚኖራቸው ኣገር ኣፍራሽ ተቃዋሚ ሓይሎች ከመገነጣጠል ከተረፈች ነው።) ከምክንያቶቹም መሓከል ኣንዱ በኢትዮጵያ የተካሄደው የህወሓት/ኢህወደግ የሕዝቦች የዲሞክራስያዊ የፖለቲካ መብቶች ንቅናቄ ከጀብሃና ሻዕብያ የነፃነት ንቅናቄ ዓይነተኛ ልዩነት ኣለው። ኢሳያስ ኣፈወርቂ ኤርትራን ወደ እስርቤት ጨርሶ እስከ ቀየረበት ጊዜ ጀምሮ፣ የኤርትራ ህዝብና የሻዕብያ መንግሥት የተገኘው “ነፃነት” እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጋር የጠመደው የፍጥጫ ንሮ ራሳቸው የቻሉ ኣዋጋቢ ለውጦች ኣድርገው የተቀበሉበት ሁኔታ ነበር ያየነው። በኢትዮጵያም ቢሆን በትግሉ የተገኙት የዲሞክራስያዊ መብቶች ከመጀመርያዎቹ ኣመታት የሚያሽቆልቁልበት ምክንያቶች ተከስተዋል። ለዚህም ምክንያት የሆኑት የፖለቲካ ተዋናዮች በዲሞክራስያዊ መብቶች ጥያቄ ላይ ከማትኮር ይልቅ ከፋፋይ ፖለቲካ በመከተላቸውና በህወሓት ኣመራር ለሁለት መከፈል ለመለስ ዜናዊ ኣምባገነናዊ ስርዓት ማንሰራራት እድል ከፍተዋል። በተለይም የመሓል ኣገር ፖለቲከኞች በህወሓት/ኢህወደግ የመጣው ለውጥ ከመጀመርያውኑ ጀምሮ እንደ ብሄረሰባዊ መፈንቅለ መንግሥት እንጂ ሙሉ የዲሞክራስያዊ ለውጥ ለማምጣት ልዩ ኣጋጣሚ እንደነበረ ተገንዝበው ሊጠቀሙበት ኣልቻሉም። ኣሁንም ቢሆን ኣምባገነናዊ ስርዓት ለመቀልበስ እድሉና እንቅስቃሴው ጨርሰው ኣልተዘጉም።

ሌላው፣ በኢትዮጵያ ያለው የሕዝብ ብዛት፣ የህብረተሰብ ስብጥር፣ በየፊናቸው የሚያቀርቡት ከፍተኛ ግፊት ያላቸው የዲሞክራሲና ሌሎች መብቶች ጥያቄ ከኤርትራው ሁኔታ ስለሚለይ ኣምባገነን መንግሥት ህብረተሰቡን በቀላሉ ለመቆጣጠር ኣስቸጋሪ ያደርገዋል። በኢትዮጵያም ከኤርትራ በበለጠ ለዲሞክራሲ ምሥረታ የሚበጁ ተቋማት፣ ለምሳሌ የፖለቲካ ድርጅቶች (የተፍረከረኩም ቢሆኑም)፣ በተሻለ ደረጃ ይገኛሉ። ይህ የዲሞክራስያዊ መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ እነሆ ከ1966ቱ የተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ኣላቋረጠም። ስለዚህ በኢትዮጵያና ኤርትራ የዲሞክራስያዊ ስርዓት ምሥረታ ተመሳሳይ የጊዜ ሰሌዳ እንደሚኖራቸው ኣድርጎ መገመት ያስቸግራል። ሁለቱ ኣምባገነኖች ቢወገዱም፣ ወደ በኋላ እንደምናየው፣ ሁለቱም ኣገሮች በሚጠበቀው ኣኳሃን ወይም ጊዜ ውስጥ ዲሞክራስያዊ ካልሆኑ የፌደሬሽን ወይም ኮንፌደሬሽን ስምምነት ውስጥ መግባት እጅግ ኣዳጋች ያደርገዋል። በእርግጥ በኢትዮጵያ ዲሞክራስያዊ መንግሥት

መሠረት ከተቻለና የኢሳያስ ስርዓት በለዘብተኛ መንግሥት ከተተካ (ዲሞክራስያዊም ባይሆን) የውህደቱ እድል የሰፋ ይሆናል።

ዳንኤልና ተስፋፅዮን በፅሁፋቸው እንዳቀረቡት በታሪክ ተፃራሪ ስፍራዎችን ይዘው ሲማጎቱ ኣይተናል። ተስፋፅዮን ለወቅታዊው ችግር ጠራጊ መንገድ መፍትሄ ሓሳብ ሳያስቀምጡ፡ (ለምሳሌ የድንበር ግጭት መፍትሄ፣ የኢትዮጵያ የዓፋር ቀይ ባህር መሬቶች ጥያቄ፡ በመሠረቱም የኤርትራ የመገንጠል ህጋዊነት ጥያቄ፡ ወዘተ) ለግንኙነቱ ሂደት ጅምር ካለንበት ሰዓት የሁለቱ ኣገሮች ኣዳጋች ችግሮች ኣንገብጋቢነት ኣኳያ ይመለከቱታል። እንዳሉትም "ምንም እንኳ ኤርትራ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኣባል የሆነች ሉዓላዊት ኣገር ብትሆንም፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግኑኝነት በይዘቱም በመልኩም ገና ፈፅሞ ኣልተደለደለም ማለት ይቻላል።" እዚህ ላይ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ካሉዋት ያልተፈቱ ሉዓላዊ ጥያቄዎች ኣኳያ ስንመለከት ይህ ገና ያልለየለት ግኑኝነት የኤርትራ ሉዓላዊነትንም ጭምር ጥያቄ ውስጥ እንደሚያስገባ ሆኖ እመለከተዋሎህ።

ዳኒኤል በበኩላቸው የጊዜ መነሻቸው ከንጉሥ ሃይለሥላሴ የክፍለሃገሮች ኣወቃቀር ይጀምራል። የሚሟጎቱለት የፌደሬሽን ዓላማ እንዲሳካ የኢትዮጵያ ኣስተዳደር ወደ ድሮው የ14 የክፍለሃገራት ኣወቃቀር መመለስ ኣለበት ይላሉ። እንድያዉም ለዚህ መነሻ የሚያደርጉት መሠረተ-ሃሳብ በቆዳ ስፋትና ህዝብ ብዛት የማይመጣጠኑ ክፍለሃገራት ፌደሬሽን ሊሳካላቸው ኣይችልም የሚል ነው። "ፌዴሬሽን የሚሰራው ኣባል ክፍለ ሃገራት በመሬት ስፋትና በህዝብ ብዛት ተመጣጣኝ ብዙ ሲሆኑ ነው። ለዚህም ብዙ ኣገሮችን መጥቀስ ይቻላል። ኣሜሪካ፡ ካናዳ፡ ህንድ፡ ... ወዘተ።" በማለት ኣብነትም ያቀርባሉ።

በመጀመርያ ይህ ኣብነት ከነመሠረተ-ሃሳቡ ጭምር የተሳሳተ መሆኑ መረጃ ላቅርብ፣ በፌደሬሽን የሚወሃዱ ክፍለሃገራት የግድ በቆዳ ስፋትና ህዝብ ብዛት ተመጣጣኝ መሆን የለባቸውም። የሳቸው ኣመለካከት መንስኤ የመንግሥት ስልጣንና ሃብት ክፍፍል ሚዛን ሊኖሮው ኣይችልም የሚል እምነት የተመረኮዘ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ከተባለማ ክፍለሃገራቱ ሁለገብ የሆነ በተመሳሳይ ፀጋ የታደሉ እንዲሆኑ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው። ፌደሬሽን ታድያ ለምን ኣስፈለገ? ፌደሬሽን የሚያስፈልገው (የህዝቦች የታሪክና ደም ትስስር እንደ ውህደት ቅድመ ሁኔታ እንኳ ብንተወው) ክፍለሃገራት የበኩላቸውን ሃብትና ፀጋ በማዋሃድ የወደፊት የጋራ እድላቸውና ብልፅግና የሚያሻሽሉበት ውህደት ነው። ይህም የሚረጋገጥበት መንገድ በፌደራል መንግሥትና በክፍለሃገራት የስልጣን ክፍፍልና የኣገሪቱ ሃብትን በጋራና እኩልነት መከፋፈልን በሚደነግግ የኣገሪቱ ህገመንግስት ኣመካኝነት ነው። ለምሳሌ ብንወስድ ከ60% በላይ የካናዳ ህዝብ የሚኖረው ከኣስሩ ክፍለሃገራት በሁለት የኦንታርዮና ኩቤክ ክፍለሃገራት ነው። የሁሉም ክፍለሃገራት ሃብትም ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ገቢን በእኩልነት በማከፋፈል ኣቅመ ደካማ ክፍለሃገራት ከማእከላዊ መንግሥት እንዲደጎሙ ያገሪቱ ህገመንግሥት ይደነግጋል። ትላንት ኣትራፊ የነበረ ክፍለሃገር ዛሬ ተደጓሚ ሊሆን ይችላል፣ በኢትዮጵያ ያለ የድሃና ሓብታም ክፍለሃገራት ብኩን ኣስተሳሰብ ለማረም ያህል ማለቴ ነው። ለነገሩ በኣሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ክፍለሃገራት ድሃና ሓብታም ተብለው የሚለዩበት ሁኔታ የለም። ሁሉም በውጭ እርዳታ ተደጓሚዎች ናቸው።

አመሪካን ብንወስድ ደግሞ ከ54% በላይ ህዝብዋ የሚኖረው ከ52ቱ በ10 ክፍለሃገራት ብቻ ነው። ካሊፎርንያ በ2001 ቆጠራ መሠረት 12.11% የህዝብ ብዛት ሲኖራት የዋዮሚንግ ክፍለሃገር ህዝብ 0.17% ወይም ከግማሽ ሚልዮን ያነሰ ነው። የካሊፎርንያ ግዙፍ ኢኮኖሚ እንግዲህ ከኣለም 6ተኛን ስፍራ የያዘ ነው።

## የኮንፌደሬሽን ግኑኝነት ቅድመ-ሁኔታዎች

የዲሞክራስያዊ ስርዓት መመሥረትና የማህበረ-ፖለቲካዊ እንቅፋቶች መወገድ እንዳሉ ሆነው፣ የኮንፌደሬሽን ወይም የፌደሬሽን ውህደት ለመፍጠር መሠረታዊ የቅድመ-ሁኔታዎች ልዩነት እንደሚኖሩ እንገነዘባለን። ኮንፌደራሽንን ብንመለከት፣ በሁለቱም ኣገሮች መሃከል የሉዓላዊነት እውቅና እንዲኖር ያስፈልጋል። ለኤርትራ የሚያደላና እንድያውም ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ በመለስ ዜናዊ የሚመራ መንግሥት ሳይሆን፣ የኣገሪቱን ሉዓላዊነትና ጥቅም የሚወክል መንግሥት (ዲሞክራስያዊ ሆነም ኣለሆነ) ሥር ሆነን እንነጋገር ብንል ሁለቱም ኣገሮች የተለያዩበት ሁኔታና በገቡበት “የድንበር” ጦርነት ቀውስ ምክንያት፣ ኢትዮጵያ ኤርትራን የሉዓላዊነት እውቅና ልትሰጣት ኣትችልም። በተለይ የሁለት እኩያ ሉዓላዊ መንግሥታት ስምምነት የሚጠይቅ ኮንፌደሬሽን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የማይጋጭና የማያወላዳ የሉዓላዊነት ህልውና እንዲኖራት ያስፈልጋል። ኤርትራ ከኢትዮጵያ በኣመፅና ሕገወጥ ኣገባብ መገንጠልዋ ራሱ ያልተፈቱ ወይም ያልታረቁ ችግሮች እንዳሉ ኣመላካች ነው። በእርግጥም ኣሉ። ኤርትራ በኣሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ይህ የሉዓላውነት እውቅና የላትም። ምክንያቱም ኣንደኛ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ውክልና ባልተሰጠውና የኣገሪቱን ሕገ-መንግሥት ባልተከተለ መንገድ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ኣካል የነበረችውን ኤርትራ ማስገንጠል ወይም እንድትገነጠል መፍቀድ እንደገና መታየት የሚኖርበት ሕገወጥ ድርጊት ነው።

ስለ ኤርትራና ሉዓላዊነትን በተመለከተ ግልፅ መሆን ያለበት ነገር የመሰለኝን ኣስተያየት ልጨምርበት። ኤርትራ ለመገንጠል የበቃችው በኢትዮጵያና ሕዝብዋ ላይ የሻዕብያ ከባድ የጥላቻ ዘመቻ እንዲሁም በኣስኰናኝና ኣእምሮ-ቢሱ ደርግ የረጅም ጊዜ የፍጅት ጦርነት እንደሆነ ይታወቃል፤ ተከትሎም፣ ያለው የመለስ ዜናዊ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳያሳውቅ እንዲሁም ስለ ተገነጠለችበት ኣኳሃን ምንም ዓይነት ይፋ የሆነ መንግሥታዊ የስምምነት ሰነድ በሌለበት በሚስጢርና በሽፍጥ ነበር የተገነጠለችው። በዚህ ላይ ሁለት ነገሮች ማንሳት ይቻላል፤ ኣንዱ፣ ጦርነት ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ርቱዕ መፍትሔ ነው ወይ? የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የተከናወነ ወይም ህዝቡ የወሰነበት የሉዓላዊነት ማረጋገጫ መንግሥታዊ ስምምነት የት ኣለ? የሚሉ ናቸው። በመጀመርያው ደረጃ ለሌላ ግጭት መንስኤ የሚሆኑ ምክንያቶች ካሉ፣ ጦርነት ለሉዓላዊነት መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ከወዲሁ ማረጋገጥ ይቻላል። ከኤርትራ ጋር በሚከሰት ሌላ ግጭት የሚካሄድ ቀጣይ ጦርነት ወይም የተባለውን ሉዓላዊነት ለመቀልበስ የሚደረግ ሌላ ጦርነትም ራሱ የቻለ ኣንፃራዊ መፍትሄ ይሆናል ወይም ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት ነው። ስለዚህ ጦርነት የሉዓላዊነት ወይም የነፃነት ጥያቄ የፍፃሜ መፍትሔ ሊሆን ኣይችልም። ሁለተኛው ጥያቄ በተመለከተ ያለው

መንግሥት በፈፀመው ኣገርን የመቁረስ ወንጀል ምክንያት ኤርትራን በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የሚያሰጣት ሕጋዊ ሰነድ ሊያቀርብ ኣይችልም።

በተጨማሪም፣ ኣገሮች ለኣንድ የተገነጠለች ኣገር እውቅና ሲሰጡ የተናጠልና የውስጥ ፖለቲካዊ ውሳኔ እንጂ የተባበሩት መንግሥት በቀዋሚነት የሚጠቀምበት መስፈርት ኖሮት ውሳኔ በማድረግ ይህች ኣገር ሉዓላዊ እውቅና ይገባታልና እንስጥ ብሎ በቅድምያ ሉዓላዊነትን ኣያውጅም። መስፈርትም የለውም። የታይዋንን ሁኔታ ብንወስድ ከዚህ የተለየ ኣይደለም። ታይዋን ሉዓላዊት ኣገር ኣይደለችም። ራስዋን ችላ ግን ትተዳደራለች፤ ታይዋን በእንጥልጥል እንዲህ የቀረችበት ሁኔታ ከኢትዮጵያና ኤርትራው ታሪክ በመሠረቱ ይለያል። ነገር ግን ታይዋንና ቻይና እንደ ኢትዮጵያና ኤርትራ ኣንድ ኣካል የነበሩ እንደመሆናቸው ለወደፊቱም ዕድልዋ የሚወሰነው በሌሎች ኣገሮች ወይም በተባበሩት መንግሥት ሳይሆን በቻይና እጅ እንደሚሆን ነው። ቀኑ ሲለይለትም እንደ ሆንግኮንግ ከቻይና ጋር ተመልሳ እንደምትቀላቀል ኣዝማምያው ያመለክታል። እንግዲህ ለምን ኣገሮች ታይዋንን የሉዓላዊነት እውቅና ኣልሰጥዋትም የሚለው ጥያቄም ማንሳት ኣስፈላጊ ይሆናል። ሶማሊ ላንድ ለምን ከሶማልያ ሉዓላዊ እውቅና እንዳላገኘችም ሌላ መጤን ያለበት ኣብነት ነው። ኤርትራን በተመለከተ፣ የኢህወደግ መንግሥት የኤርትራ ነፃነት ኣዋጅ ገና ከደርግ ውድቀት ማግስት ውድቅ ቢያደርግ ኖሮ፣ የኤርትራ ሉዓላዊነትና መገንጠል በድንበሩ ጦርነት ወይም ከዛ በፊት ማብቃት ይቻል ነበር። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሓይሎች ኤርትራ መሬት ዘልቀው በገቡበት ወቅትም ብዙ የምዕራባውያን ሃገራት ፍፃሜው ይህ ሊሆን እንደሚችል ግራ የተጋቡበት ጊዜ ነበር።

ወደ ቅድመ-ሁኔታው ልመለስና፣ ቀደም ሲል የጠቀስኩት ቀዳሚ ምክንያት መልስ ካገኘ፣ ሁለተኛው መፈታት ያለበት ጉዳይ የኢትዮጵያ የዓፋር ቀይ ባሕር ሉዓላዊ መሬቶች ጥያቄ ነው። ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱበት ቢቻል በሰላማዊ መንገድ መፍትሂ መገኘት ይኖርበታል። ከዚህም በተያያዘ፣ ኤርትራ ከመገንጠልዋ በኋላ በውል ያልተለየውና ገና ያልተፈታው የድንበሩ ጦርነት ሌላ ፈር መያዝ ያለበት ቅድመ-ሁኔታ ነው። እነዚህ በኣጠቃላይ ገና የኤርትራ እጣ-ፋንታ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ስለ ሉዓላዊነትዋ ጥያቄ ስር-ነቀል ለውጥ የሚያስከትሉ ክስተቶች ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ቅድመ-ሁኔታዎቹ ለኮንፌደሬሽን ስምምነት እጅግ ወሳኝ የሚያደርጋቸው ሌላ ምክንያት ኣለ። ይኸውም፣ ኮንፌደሬሽን ለውህደት ተስፋ የሚደረግለት ቃልኪዳን ቢሆንም ለቀዋሚ ውህደት ዋስትና የማይሰጥ፣ ስምምነቱ ኤርትራ እንደገና ወደ ሙሉ ሉዓላዊ ህልውና የምትመለስበት መብት የሚያስጠብቅ ውል የሚያሰፍር ይሆናል። ለምሳሌ ኤርትራ ከ20 ዓመታት በኋላ ኮንፌደሬሽኑ ኣልጣመኝም ብትል ኢትዮጵያም በኤርትራ የሚኖራት የይገባኛል ጥያቄዎችዋን ካላነሳች (ካልሰረዘች) በወቅቱ ያልተወገዱ ችግሮች ቀጣይነት ኖሮዋቸው ወደ ግጭት ያመራሉ ማለት ነው።

ኤርትራ መሬቶቹ የኔ ናቸው ብትልም ናቸው ማለት ኣይደለም። ክርክሩ ይቀጥልና ጉዳዩ ለኢትዮጵያ በሚኖረው ኣንገብጋቢነት መሠረት ዛሬም ነገም

በጦርነትም ልትፈታው ትገደዳለች። ጦርነቱ የችግሩ ፍፃሜ መፍትሄ ተደርጎ ከተወሰደ፣ የኤርትራ ዕጣ ፋንታ እዚህ መድገምም ኣያስፈልግም።

## የዳንኤል ክንዴና የመለስ ዜናዊ የዓሰብ ወደብ ሰንካላ የኣመለካከት ውህደት

ዳንኤል ክንዴ የወደብ ጥያቄ ለሚያነሱ ኢትዮጵያውያንን እንዲህ ሲሉ ይገስፃሉ፡- “ኣንድ ኣንደ በኣስተሳሰባቸው ውስን የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ጋር ያሉትን ታሪካዊ ሰንሰለቶች ሁሉ በጥሰው፤ ስለ ዓሰብ ወደብ ብቻ የተቆረቆሩ ይመስላሉ።” ይሉና ወደ ኤርትራውያን በመዞርም ባለፉት 16 ዓመታት ኢትዮጵያ ወደቦቹን ባለመጠቀምዋ “...ኢኮኖሚዋ ኣልወደቀም። ፖርትሱዳን፣ ጅቡቲ፣ በርበር፣ ሞምባሳ፣ ሶማልያ ደግሞ ሰላም ስታገኝ ኢትዮጵያ በሞቃድሾ፣ በቦሶሶ እና በኪስማዩ ወደቦች መጠቀም ትጀምራለች።” ይላሉ። ፕሮፌሰር ዳንኤል ሌሎች ኢትዮጵያውያን የሚሉትን መቀበል ቢችሉ እሳቸውም ሓሳባቸውን መግለፃቸው በውይይት መቀራረብ ስለሚቻል እጅግ ተፈላጊ ነው። ችግሩ የሌሎችን ሓሳብ በጭፍን ላለመቀበል በመወሰን ሰዉን ሲዘልፉ ይታያሉ። በተለይ የኢትዮጵያን የወደብ ሁኔታ በዚህ መልክ ስያስቀምጡ፣ የካድሬ ፖለቲካዊ ባህል ከሚያራምዱ መለስ ዜናዊና ተከታዮቹ እንዲሁም ኣምሳያዎቻቸው ኣክራሪ ከሃድያን ተቃዋሚዎች ከሚገኙበት የእብዶች ሰፈር መውረዳቸውን ያሳያል። እንዲህ ዓይነቱ የተምታታ ኣስተሳሰብ ያላቸው ምሁራን ናቸው እንግዲህ የኣምባገነኖች መገልገያና ባሮች ሆነው የኢትዮጵያ ህልውና በዛው መጠን የሚያወሳስቡት።

እዚህ ላይ ስለሚሉተ ጉዳይ ክብደት ልብ በሉ፣ እሳቸው የሚሉት መለስ ከሚለው የክህደት ወሬ በምንም ኣይለይም። ሌሎች የባእድ ወደቦች መጠቀም ይቻላል ሲሉ፣ ኣንደኛ የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ መሬቶች ለኤርትራ ኣሳልፈው ሰጥተዋል፤ ሁለተኛ፣ ፕሮፌሰር ዳንኤል እንደ መለስ ዜናዊ ወደብን የመሰለ የኣገር ማንቁርት በማናናስ ተለዋጭ የግልጋሎት እቃ ኣድርገው ኣቅርበውታል። “ሓደን ብጉርሑ ሓደን ብገርሁ” የሚባል የትግርኛ ኣባባል ኣለ፤ መለስ በብልጥነቱ መሆኑ ነው የገዛ ኣገሩ በሰንካላ ኣመለካከቱ ከንቱ ያደረጋት፤ እሳቸውም ደግሞ “ሁሉም ኣውቃሎሀ” በሚል ትዕቢት ይሁን በሌላ መገመት በሚያዳግተኝ ምክንያት፣ እንዲህ የሚሉት።

እሳቸው የሚሉት መለስ ዜናዊ ከሚለው በቀጥታ የተቀዳ ነው። በኣንድ ወቅት ኤርትራ “ወደቦችዋ የገመል መጠጫ ትጠቀምበት” ብሎ ኣፌዞኣል፣ በተከታታይም “ወደብኮ እንደ ማንም ዕቃ የግልጋሎት ተለዋጭ ዕቃ ነው፤ የግሎባላይዘሽን ዘመን እኮ ነው”፣ ወዘተ በማለት መኣምረ-ኩሉ ሆኖ በየቃለ መጠይቁ ሲለፈልፍ ይውላል። የትኛዋ ኣገር ናት ግሎባላይዘሽን የሚባል ነገር መጥቶኣልና ወደቦችን እንቀያየር ወይም ለጋራ እንጠቀም ያለችው? እንዲህ የመሰለ ኣንደበት ከኣንድ የኣገር መሪ ያለምንም ሰበብ ሲነገር ኢትዮጵያ ባለችበት ኣሳፋሪ ሁኔታ መገኘትዋ ብዙም የሚደንቅ ኣይደለም። የባሰውም ነገር ሌሎች ኢትዮጵያውያን የዚህ የክሕደት ኣስተሳሰብ የገደል ማሚቶ ሆነው ሲቀበሉ ነው።

ወደብ እንደ ተንቀሳቃሽ ድልድይ ወደ ኣዲስ ኣበባ በር ማቅረብ ኣይቻልም። ወደብ የኣንዲት ኣገር ባሕር ገጠም የሆነ ሉዓላዊ መሬት ኣካል ነው። ወደቡም ብቻ

ሳይሆን የአካባቢው መሬትና የባሕር ሃብት ጭምር። የኢትዮጵያውያን ጥያቄም ይሀው እንጂ እንደ ቅርጫ ተቆርጣ ዓሰብ ትሰጠን አላሉም። ስለ ዓሰብ መመለስ ሲነሳ በ"ዓሰብ" ስም ሳይወሰን የቀይ ባህር ጠረፍ መሬቶች በመጥራት ጥያቄው በግልፅ መታወቅ አለበት። የቀይ ባሕር ዓፋር የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬትም ምፅዋ ድረስ እንደሚዘልቅ የታወቀ ነገር ነው።

የዚህ አስተሳሰብ ጉድለት ምንድነው ብንል፣ ዳንኤል ክንዴ የኢትዮጵያና ኤርትራ "ሰንሰለታዊ" ግኑኝነትና የዓሰብ ወይም ዓፋር ቀይ ባህር መሬቶች ርቱእ የሆነ ዝምድና እንዳላቸው ስለሚገምቱ ነው። ይህን ለሙግት ማቅረብ ርቱእ አስተሳሰብ አይደለም። ኤርትራውያን ለብቻቸው ወይም ውህደትን መረጡ አልመረጡ፣ ከቀይ ባህር ጠረፍ መሬቶች ጥያቄ ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም። በተለይም አለ የሚሉት ዝምድናም በዓላማ ወይም በመንፈስ የተበላሸ ነው።

ሰንሰለቱን መበጣጠስ በተመለከተ፣ እሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ሕዝብ አላስገነጠላትም፤ ያስገነጠሉት ደርግ፣ የደርግ ከፋፋይ ካድሬዎችና አክራሪ ብሔርተኛ የሕብረተሰብ ክፍል፣ የወያነ መሪዎች፣ ሻዕብያና ሻዕብያን የተከተለ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ናቸው። የኤርትራ ሕዝብ ራሱ የበጣጠሰው "ታሪካዊ ሰንሰለት" የኢትዮጵያዊ ጉዳይ መሆን የለበትም። የኢትዮጵያዊ ጉዳይ የኤርትራን ታሪካዊ ሰንሰለት ለመጠገን መለማመጥ ሳይሆን በቅድምያ የገዛ አገሩን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ነው። ታሪካዊ ሰንሰለቱ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ከሆነ ኤርትራዊን እንቅልፍ ይንሳው። ኤርትራም እንደገና መወሃድ የሚትችለው የኤርትራ ሕዝብ መብት ተከብሮ ፍላጎት ሲኖረው ነው። የምትወሃድበት ጊዜም በ10 ዓመት ውስጥ ላይሆንም ይችላል። እስከዛ ድረስ ግን ኢትዮጵያ ኤርትራ ትቀላቀል ይሆን ወይ እየተባለ በተስፋ በመጠበቅ የቀይ ባሕር ሉዓላዊ መሬትዋን ሳታስመልስ የሚሆን ነገር አይደለም። ኢትዮጵያ የመለስ መንግሥት በአጭር ጊዜ አስወግዳ መሬቶችዋን ካላስመለሰች በቀር ሁለመናዊ ሉዓላዊነትዋ ስጋት ላይ ወድቆአል። ጠበኛ ከሆኑ ጎረቤት አገሮች ወደብ በመለመን ልትዋጣው ስለማትችል መበታተን ላይ ልትደርስ ትችላለች። የኢትዮጵያን የውጭ ደህንነትና አንድነት በፅናት ለመጠበቅም የቀይ ባሕር መውጫ በርዋ ማስመለስ ወሳኝ ነው።

ስለ የውጭ ንግድ ሲያወሩ "ምፅዋ ቡናውን ለማድረስ የሚከፈለው የትራንሰፖርት ወጪ ብዙ ስለሚሆንና ከቡናው ዋጋ ላይ መጨመር ስላለበት የቡናውን ዋጋ በጣም ከፍ ስለሚያደርገው ገዥ ያጣል። በጁቡቲ፣ በበርበራ፣ በሞቃድሾ እና በሞምባሳ መጠቀም ያዋጣል።" በማለት ይተነትናሉ። ሞቃድሾን እንደ አማራጭ ጠቅሰዋል፤ እግዚአብሄር ሕሊና ይስጣቸው ከማለት ምን ልበል። አረብ አገሮች የሚቆጣጠሩት የጂቡቲ ወደብ ችግሩ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ወደብ ቢኖራት ኖሮ የአንድ ቢልዮን ዶላር ግድም የጅቡቲ ወደብ አመታዊ ወጪ አገሪቱን ከ30 አመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የማይቀለበስ ወሳኝ ኢኮኖምያዊ እድገት እንደሚያስገኝላት በእርግጠኛነት መናገር በተቻለ ነበር።

ቡናን ከምፅዋ በሞምባሳ ወደ ውጭ መላክ ዋጋው እንደሚቀንስ ለማስረዳት ሞክረዋል። የፕሮፌሰሩ የቡና ገበያቸው የት እንደሆነም አይገባኝም። ዋናው

የኢትዮጵያ ገበያ ግን በሰሜን ወደ ኣውሮጳና ምስራቅ ወደ ኤሽያ ነው፤ በደቡብ ኣይደለም። የየብስ ጉዞ በጨመረ ቁጥርም የመጓጓዣ ዋጋ ከባህር ይልቅ በንረት ይጨምራል። ለምሳሌ በካርታ ከታች እንደሚታየው፣ ከኣዲስ ኣበባ እስከ ኣውሮፓ የሚያሳየው ቀይ መስመር ርቀት 5.5 ሰንቲ፡ሜትር ሲሆን በሞምባሳ የሚሄደው ሰማያዊ መስመር ግን 9 ሰንቲ፡ሜትር ነው። እኔ የማይገባኝ ነገር የ5ኛ ክፍል ተማሪ በቀላሉ የሚረዳው ነገር፣ እያወቁ ኢትዮጵያ ያለችበትን ኣስቸጋሪ ሁኔታ በግድየለሽነት የሚያቃልሉት ለምን እንደሆነ ኣይገባኝም። ወይስ ኤርትራኖች በዚህ ተሞኝተው "እንግድያውስ እሺ" ሊሉዋቸው ይጠብቃሉ? ከሳቸውና ከመለስ ዜናዊ ትንተና ምኑን ከምኑ ይመረጣል? መለስ ዜናዊ ሕሊናችንን የሚፈታተነን በበቃ ነበር፤ ይህ ኣይነቱ ኣስተሳሰብ የሚያሳየው ነገር ቢኖር የፖለቲካዊ ኣመለካከትን የሚያወላግድ በሽታ የያዛቸው ጥቂት ያልሆኑ የኢትየጵያ ምሁራን በቀጥታ የማሰብ ችሎታቸው የከሰረና ከእውነታ ጋር የተለያዩ መሆኑ ኣመልካች ነው።

ፕሮፌሰር ዳንኤል ስለ ኤርትራ የግኑኝነት ጥያቄ፣ የዓለም ንግድ፣ የምስራቅ ኣፍሪቃ ሁኔታ ለኣገሪቱ ያለው የደህንነት ኣስጊነት እና ሌሎች ችግሮች በትክክል ያልተረዱት ኣለበለዝያም ሆን ብለው የሚያምታቱት ለምን እንደሆነ ግራ የሚገባ ስለሆነ ራሳቸው መግለጫ ቢያቀርቡበት ተገቢ ይመለኛል።




**ኮንፌደሬሽን በኢትዮጵያ የሚያስከትላቸው መዘዞች**

**ለሕገወጥ ግንጠላ ሕጋውነት መስጠት፦** በመጀመርያ፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ህልውና ያለው ከሓዲ መንግሥት በኤርትራ ቁጥጥር ስር በማስገባቱ ኣገሪቱ ሉዓላዊነትዋን ከምትጋፋ ኣሁን ኤርትራ ከተባለች ኣገር ጋር ስምምነት መግባት ይህንኑ የክሕደት ተግባር ሕጋዊነት መስጠት ያክል ይሆናል።

**የመዥገርና-በሬ ግኑኝነት፡-** ሁለተኛ፣ ከኤርትራ ጋር በኮንፌደረሽን ይቅርና በፌደረሽን ስምምነት መግባት ለኢትዮጵያ ጉዳት እንጂ ምንም ያክል ጠቀሜታ ኣይኖሮውም፤ ኮንፌደሬሽን ሁለት ኣገሮች ለሉዓላዊ ጥቅማቸው በየፊናቸው የሚገቡት የቅንብር ስምምነት እንጂ እንደ ፌደረሽን ሁለመናዊ ፀጋቸውና

ጉልበታቸውን በማሰባሰብ ብልፅግናን የሚጎናፀፉበት ኣንድ ወጥ መንግሥታዊ ስርዓት ኣይደለም።

በኮንፌደሬሽን ምሥረታ የኢኮኖሚና የንግድ ስምምነት ወደ ጎን የማይተው ለኤርትራ በተለይ በኣሁኑ ወቅት የሞትና ሂወት ጥያቄ ነው። ለምሳሌ ኣንድ ወጥ ገንዘብ መጠቀም (ናቅፋ ቀርቶ ብር ማለት ነው) ለኤርትራ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚኖረው ይሆናል። ካለችበት የቁጠባ ቀውስም ሊገላግላት ይችላል። እጅግ ውድ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ ቁሳቁስ የራስዋን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ሳያስፈልጋት ከኢትዮጵያ የመጠቀም እድል ይሰጣታል።

በንግዱ ዘርፍ ስንመለከት፣ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ኢኮኖሚያዊ ኣቋም፣ የምርት ውጤትና የፍጆታ ኣቅም የላቸውም። ስለዚህ ግኑኝነቱ እጅግ ሚዛናዊ ያልሆነና የጥቅም ክፍፍል መዛባትን ችግር የሚያስከትል ይሆናል። ኤርትራ የሚፈለገው የምርት ወይም የፍጆታ ኣቅም ስለሌላት ማድረግ የምትችለው ከጦርነቱ መቀስቀስ በፊት እንዳየነው የኮንትራባንድ እቃዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማጕረፍና የኢትዮጵያ የእርሻና እንዱስትሪ ምርቶች እንደ ራስዋ ምርት ለውጭ ምንዛሪ መላክ ይሆናል። ይህም ዓይነት በጣም ጎጂ የሆነ የኢኮኖሚ ግኑኝነት ውጤት በጦርነት መልኩ መስዋዕት ተከፍሎበታል። በተወሰኑ የኢኮኖሚ ግኑኝነቶች ስምምነት ጥብቅ የሆነ የድንበር ንግድ ቁጥጥር ቢደረግ እንኳ ለኣስተዳደሩ ኣስቸጋሪና የሚያስፈልገውም ወጪ ፋይዳቢስ ያደርገዋል። ስለዚህ ኤርትራ በኮነፌደሬሽን መቀላቀል ለኢትዮጵያ ምንም ጥቅም የሌለውና ይልቁንም እጅግ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ጒዳትና መዘዝ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትል ይሆናል።

ፀረ-ውህደታዊ መርህ የመከተል ስነልቦና፦ በተለይም የኤርትራ ማህበረሰባዊ የስነልቦና፣ የታሪክና፣ ማንነታዊ ቀውሶች እስካልተወገዱ ድረስ ውህደት የሚባል ነገር መዘዙ የበዛበት ይሆናል። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ ከኢሳያስ መንግሥት በኋላ በኤርትራ የሚኖር ኣምባገነናዊም ይሁን ዲሞክራስያዊ ስርዓት፣ ባለው ኣሉታዊ ማህበራዊ ስነልቦና ምክንያት ፀረ-ፌደራላዊ ኣቋም የሚኖረውና ለሚፈጠርለት ልዩ የኢኮኖሚና ሌላ ጠቀሜታ ብቻ ሲል ፖለቲካዊ ውህደትን የማይጨምር ኮንፌደረሽን የሚመርጥ እንደሚሆን መተንበይ ይቻላል።

ኤርትራን ከሌሎች ፌደራላዊ ኣገሮች ሁኔታ ለማነፃፀር ያህል፣ ለምሳሌ ኩቤክ በካናዳ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ የፌደሬሽኑ መስራች ክፍለሃገር ብንወስድ ሁለቱ የክፍለሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች እስከ ዛሬ ያላለቀለት የመገንጠል ሕጋዊ እንቅስቃሴ ያካሂዳሉ። የፓርቲ ኩቤክዋ ክፍለሃገራዊ መንግሥት ክፍለሃገርዋን ከካናዳ ጨርሶ ለመገንጠል ሕዝብ ስለማይደግፍ የማይሳካለት ነገር ስለሆነበት በ1980 ፈረንጅ ሉዓላዊ-ውህደት ወይም (sovereignty association) የተሰኘውን የሕዝብ ድምፅ ውሳኔ ኣካሂዶበት ነበር። ይህ ዓይነት ግንጠላ የኩቤክ ሕዝብ ውሳኔ 60% ውድቅ ስላደረገበት ሊሳካ ኣልቻለም። (ቢያፀድቀውም ኖሮ ካናዳ ትቀበለው ነበር ማለት ኣይደለም፤ ኩቤክን ለውጭ ዘግታ በማስቀረት በብዙ መንገዶች ውድቀት ሊደርስባት በቻለ ነበር።) ሉዓላዊ-ውህደት ከፖለቲካዊ ሉዓላዊነት በቀር ኣብዛኛው የኢኮኖሚ ግኑኝነት፣ ኣንድ ወጥ ገንዘብና ድርብ ዜግነትም የሚጨምር ሊሆን ይችላል፣ ከሞላ ጎደል ኣንድ ኣገር ማለት ይቻላል።

ኢኮኖምያዊ ግኑኘነትን በተመለከተ ይህ ዓይነት የሉዓላዊ-ውህደት ቀጣይ ግኑኘነት ኤርትራ ከምትፈልገውና ከሚታለምለት የኢትዮጵያ ግኑኘነት ጋር ኣምሳያነት ሲኖረው፣ ኮንፈደሬሽን ደግሞ ፍፁም ነፃ የሆነ የሉዓላዊ ፖለቲካዊ ነፃነትና መብት የሚሰጣት ሆኖ እናገኘዋለን። ቅድም እንደጠቀስኩት፣ በኤርትራ በኩል ግኑኘነቱን የሚሻ መንግሥትም ከሁለቱም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅሞች የሚያጣቅስ ማለትም በኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ግኑኘነትና ፖለቲካዊ ሉዓላዊነትን የሚያጣቅስ ለኤርትራ እጅግ የሚረባ ለኢትዮጵያ ደግሞ ባንፃሩ የሚጎዳ ኮንፈደሬሽን የሚባል መርህ ሊከተል ይችላል።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ግን ኩቤክና ኤርትራ በኢኮኖምያዊ እድገት ይሁን በሌላ መመዘኛዎች በፍፁም ሊወዳደሩ የማይችሉና ኩቤክ ብትገነጠል ያለ ምንም ችግር ራስዋ ችላ መተዳደር የምትችል ኢንዱስትሪያዊት ኣገር እንደምትሆን ነው። መገንጠል የሚያስከትሉት ብዙ ችግሮች ስላሉ ግን የመወሰን መብት ያለው ሕዝብ ለሁለተኛ ጊዜ በ1992 ፈረንጅ ውድቅ ኣድርጎታል። የመገንጠሉ ሕጋዊ ፍፃሜ ግን በክፍለሃገሩ ሕዝብ ብቻ ሳይወሰን በኣገሪቱ ሕገመንግሥት ደንብ መሠረት ብዙ ውጣ-ውረድ የሚጠብቀው ራሱ የቻለ ሂደት ነው። የግንጠላዉን ድርድር ለማከናወንም ራሱ የቻለ የካናዳን ሕገመንግስት ለውጥን ይጠይቃል። ኤርትራና ኩቤክን ብናወዳድር ሁለቱም በታሪክ ለኢትዮጵያና ካናዳ ያላቸው ግኑኘነት እጅግ የተለያየ ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ኣንድ ኣካል፣ ታሪክና ባህል ያላት ክፍለሃገር ናት ወይም ነበረች። ኩቤክ ግን ፈረንሳዮች ከእንግሊዞች በተስፋፊነት ግጭት በሰሜን ኣመሪካ ከመገናኘታቸው በቀር በባህልም ታሪክም ኣይገናኙም። በስነልቦናና ንቃተሂሊና ሲወዳደሩ፣ የኩቤክ ህዝብ መገንጠልን ኣይደግፍም፣ የሚያዋጣውንም የመወሰን እውቀትና መብት ባለቤት ነው፤ ኤርትራ ግን በጥላቻና ጠበኝነት ስነልቦና ሰበብ መቀራረብን መስበክ ይቅርና ስለ ስለሚያዋጣት ጉዳይ ላይ ለኣንድ ኣፍታ እንኳ ጥሩ ውሳኔ ላይ ደርሳ ኣታውቅም።

የቀይ ባሕር ዓፋር መሬት በኤርትራ እጅ ስለ ማስቀረት ክጀላ፦ ኮንፈደሬሽን በሌላ መስተዋት ብናየው ሌላ መልክ ይዞ እናገኘዋለን፣ እንደ ተስፋፅዮን መድሃንየ ኣባባል፣ በኤርትራ እጅ ያሉትን ወደቦች እንደባለቤት በቁጥጥርዋ ስር ይቀራሉ። በሚደረግ የኮንፈደሬሽን ስምምነትም ኤርትራ የኢትዮጵያ የውስጥ ገበያ ተጠቃሚ ለመሆን እነዚህን ወደቦች እንደ ወሳኝ የመደራደርያ ቁልፍ መሣርያዎች መጠቀምዋ ኣይቀርም። ኢትዮጵያ በኤርትራ ሥር በገዛ እጅዋ ጥገኛ ግኑኘነት ትመሠርታለች ማለት ነው። የዚህም ውጤት በ1990ው “የድንበር ግጭት ጦርነት” ታይቶኣል። መለስ ዜናዊ ራሱ በነሓሴ መጀመርያ ለኣስመሪኖ ድረገፅ በሰጠው ቃለመጠይቅ ለመጀመርያ ጊዜ ያመነበት ጉዳይ ጦርነቱ የኢኮኖሚ ውዝግብ ያስነሳው እንጂ የድንበር ውዝግብ እንዳልነበረ ነው። የኤርትራ የፖለቲካ ከበርቴዎች ብቻ ሳይሆኑ በክልሉ ያሉ ሁሉ፣ እንደ መለስ ኣገላለፅ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖር የፈለጉት ግኑኘነት በምዝበራ፣ ሌብነትና ቅጥፈት የተሞላው ኣስተሳሰብ የተመሠረተ መኖሩ ያመለክታል። መለስም ግኑኘነቱን እየጠጋገነ ሊያኖረው እማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ተበጥሶበታል።

ለኤርትራ እጅግ አንገብጋቢ የነበረ፣ ሆኖ ያለና የሚሆን ችግር የኢኮኖሚ ችግር እንጂ የውስጥ ፖለቲካ አስተዳደር ችግርም አይደለም። ያን ችግር ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር በመሆን መፍታት ይኖርባታል። በኮንፌደሬሽኑ ስምምነት ኢትዮጵያ ይህን ዓይነቱ ውድቀት ላለመድገምና ጥቅምዋን ለማስጠበቅ እጅግ የጠበበ የንግድና ኢኮኖሚ ግኑኙነት ላይ ብቻ ስምምነት ልትገባ ትችላለች፤ የተባለለት የውሕደት ዓላማ ግን እውን ለማድረግ በቂ አይሆንም፣ በተጨማሪም የኮንፌደሬሽን ስምምነት ራሱ ለፌደራላዊ ውሕደት ቅድመ ሁኔታ ወይም አመኔታን አይፈጥርም። ምክንያቱም ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለጋራ ጥቅም የሚያበራታ መንስኤ የለውም።

ይህ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የቀይ ባሕር መሬት በኤርትራ እጅ መቅረቱ አገሪቱን ማነቆ ውስጥ ለማስገባት ካላው ስትራተጅያዊ ፋይዳ ሌላ ለኤርትራ ምንም ጥቅም ስለሌለው ዓሰብና ምፅዋ የፈረሱ ከተሞች ሆነዋል። በአሁኑ ወቅት ይልቅኑ ኤርትራ እንደ ባዕድ በመቁጠር የቀይ ባህር ዳርቻ መሬቶች የጣልያን፣ ኢራን፣ ወዘተ የመሰሉ አገሮች የኑክሌር አተላ መርዝ መድፍያና የኢንዱስትሪ ቆሻሻ መጣያ ስፍራ በመጠቀም ለትውልዶች የሚተላለፍ መቅሰፍት እየተሰራበት ነው። ነዋሪው የዓፋር ህዝብም ከቦታው “ለማፅዳት” እልቂት ሲፈፀምበት ቆይቶአል።

ዳንኤል ክንዴ እንደ ኮንፌደሬሽን አብነት ያቀረቡት ጦርነቱን ያስከተለ ብልሹ የኢኮኖሚ ግኑኙነት ውዝግብ ምክንያት፣ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ መንግሥት ባለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የኤርትራ መናኛ ኢኮኖሚ ተለጣፊ ሆኖ በመቅረቱ ለጋራ እድገት ምንም ያህል አስተዋፅኦ ስለማይኖረውና የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የቀይ ባሕር መሬቶችም በኤርትራ ሥር በመተዋቸው የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ሕልውና አደጋ ላይ በመጣል በጥገኛ ግኑኝነት ወጥመድ ውስጥ በመግባትዋ ነው። አሁንም መለስ ዜናዊ በቃለ መጠይቁ ላይ ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ሲፈፅማቸው የነበሩ ሕገወጥ ተግባራት ችላ ስንላቸው ነበርን በማለት ደጋግሞ ሲገልፅ ይሰማል (እነዚህ ተግባራት እንግዲህ የአገሪቱን ሉአላዊነት የናዱ ወንጀሎች እንደነበሩ አንርሳ)። መለስ ውስጥ ለውስጥ ያደረገው ስምምነት ሲያስፈፅም እንጂ ኢትዮጵያ ለወደፊቱ ችግር ውስጥ እንዳትገባ ሰግቶ አልነበረም። ኢትዮጵያ የወደብ በሮችዋ ስለተነፈገች ደግሞ ከኤርትራ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት መፍጠር ለተቀሩት ከህወሓት ለተባረሩት መሪዎች አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ይከተናል የሚል ስጋት በወቅቱ ያሳደረ አሳማኝ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። የቀይ ባሕር ጠረፍ በኤርትራ ሥር በመቅረቱ የሚያስከትለው ጥገኝነትና ስጋት ባአገሪቱ ሉዓላዊ ህልውናና በሕዝቡ ሕሊና ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳለው አገሪቱ አሁን ካለችበት የታገተችበት ሁኔታ መረዳት አዳጋች አይመስለኝም። ዓሰብ የኢራን ወታደራዊ ሰፈር መሆኑም የኤርትራ ህልውና፣ ራሱ የቻለ የኢትዮጵያ ቀጣይ ባላንጣነት እንደሆነ ያሰምርበታል።

ኤርትራ በውስጥ ፖለቲካ ውዝግብ የሚፈጥር በር መክፈት፦ ሌላው ኮንፌደሬሽን ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል የምለው፣ ወደ ኮንፌደሬሽን ስምምነት ስትገባ ኤርትራ በኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ የውጭ ተካፋይ በመሆን ለኢትዮጵያ ውስጣዊ ፖለቲካ መዛባትና ውዝግብ ምክንያት ልትሆን እንደምትችል ነው። በመሠረቱ የኮንፌደሬሽን ስምምነት ሲደረግ የሁለቱ አገሮች ሕገ-መንግሥት የኮንፌደሬሽኑን የዘርፍ ስምምነቶች በሚያስተናግድ መንገድ መቀየር ይኖርበታል። የኢትየጵያን

ሕገ-መንግሥት ኤርትራን በኮንፌደሬሽን ለማስተናገድ መቀየር ደግሞ የኤርትራ ጕዳይ በከፊልም ቢሆን ውስጣዊ ፖለቲካዊ ጕዳይ ያደርገዋል። ኤርትራም ሉዓላዊነትዋ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚፈጠሩት የግንባር ስምምነቶች (ለምሳሌ የመከላከያ፣ የውጭ ጕዳይ፣ የንግድ ለውጥ፣ የጋራ ገንዘብ መጠቀም፣ ድርብ ዜግነት፣ ወዘተ) ሳብያ በኢትዮጵያ ውስጣዊ ፖለቲካ የመሳተፍ ዕድሉን ይከፍትላታል። በዚህም ምክንያት የማእከላዊ መንግሥት ሥልጣን በማዳከም ወይም በመቀነስ ኤርትራ በኣገር ውስጥ ፖለቲካ ጕዳይ የመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ይጨምራል።

ኤርትራን በኣድላዊነት ማስተናገድ፦ ኤርትራን ከሌሎች ክፍለሃገራት በልዩ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ ማስተናገድ ራሱ በሌሎች ብሄረሰቦች የቅሬታ መንስኤም ይሆናል። ይህ ኣይነቱ ግኑኝነት ኤርትራ ከሚኖራት ሉዓላዊነት በተጨማሪ የኣገሪቱ ክፍለሃገራት እኩሌታ መብት የሌላቸው አንዱ ከሌላው ኣብላጫ ሓይል፣ ሥልጣን፣ ነፃነትና የጥቅም ተቋዳሽ የሚሆንበት ስርዓት ይፈጠራል። ለኢትዮጵያ የጋራ ጥቅም እጅግ በጣም ኣነስተኛ ኣስተዋፅኦ ያላት ኤርትራ ለምን የዚህን ዓይነት ኣድላዊ የሆነ ከፍተኛ መብትና ብልጫ ሊሰጣት ይገባል? ኮንፌደሬሽን እንደ የውሕደት ኣማራጭ መንገድ ብንከተል፣ ለፌደራላዊ ውህደት በጊዜ ገደብ የሚያስቀምጥ ሊሆን ይችላል። ይህን ውህደት እዉን ለማድረግ ግን ሂደቱን መቆጣጠርና ማስተዳደር እጅግ ኣስቸጋሪ ያደርገዋል። የኮንፌደሬሽን ግኑኝነት ከነ ኣካቴው የሚፈርስበትና ፌደራላዊ ውህደት ተፈፃሚነት የሚያገኝበት ልዩነት በጣም የተቀራረበ ስለሚሆን ወዴትኛው ኣቅጣጫ እያመሩ እንደሆነ መለየት ያስቸግራል።

ተስፋፅዮን መድሓንየ ሌሎች የኮንፌደሬሽን ኣገሮች እንደ ኣብነት ኣቅርበዋል፤ ሆኖም እነዚህ ኣገሮች የተመሠረቱበት ኣኳሃንና ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ወይም ኣሁን ከኤርትራ ጋር የሚታለመው ኮንፌደሬሽን ስምምነት ማወዳደር ኣይቻልም። ለምሳሌ ኣውስትራልያ፣ ስዊዘርላንደና ካናዳ ሲመሠረቱ ከዛ ቀደም ምንም ዓይነት እንደ ኢትዮጵያ የመሰለ ታሪካዊ ህላዌ ያልነበራቸውና ሲመሠረቱም ለስሙ ኮንፌደሬሽን ይባሉ እንጂ በሁሉም ፖለቲካዊ ኣወቃቀራቸው ኣንድ ወጥ ፌዴራላዊ መንግሥት ነበር። ኤርትራ ግን ኢትዮጵያ ከምትታወቅበት ታሪክ ጀምሮ ዋነኛ ኣካልዋ የነበረች ናት። ኣሁን በኢትዮጵያና ኤርትራ ኮንፌደሬሽን ይመሥረት ቢባል ያለፈውን ኣንድነትና የጦርነት ታሪካቸው ተረስቶ እንከን የሌለበትና ኣዲስ ግኑኝነት ይወጣዋል ብሎ መጠበቅ ስህተት ነው። ተደራቢና ተወዳዳሪ/ተፃራሪ የሆኑ ሁለት የኢትዮጵያና ኤርትራ ሉዓላዊ መንግሥታት በኮነፌደሬሽን ጥላ ሥር ያለ ምንም ማመንታት ጎን ለጎን መኖር ይችላሉ ብሎ ማሰብ ያዳግታል። ቅድም እንዳመለከትኩት የኣውሮጳ ወይም ሰሜን ኣመሪካ ፌደራላዊ መንግሥታት በኣንድ ማእከላዊ ፌደራላዊ መንግሥት መዋቅር ላይ የተቋቋሙ እንጂ ኣሁን በኢትዮጵያና ኤርትራ እንደሚባለው በሁለት ተደራቢና እኩያ ሉዓላዊ መንግሥታት የተመሠረቱ ኣልነበሩም። የኣውሮጳ ህብረት ራሱ ከኮንፌደሬሽን ይልቅ በብዙ ባህርያቱ ፈደሬሽን መባሉ ይቀላል፣ ከዚህም ኣንዱ በኣውሮጳ ፓረላማ ሥር የተዋቀረ በመሆኑ።

ኣገርን የማፍረስና መጠገን ፖለቲካ እንደ ኣዲስ ማስተጋባት፦ ይህም ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ኮንፌደሬሽን ምክንያት ኣገርን የማፍረስና የመጠገን እምነት ወደ ኣገሪቱ እንደገና ማስተጋባት ካለፈው የጥፋት ታሪክ ምንም የተማርነው ነገር የሌለ

ይመስል፣ ሌላ ሰበብ መፈለግ ነው። ኢትዮጵያ ስትመሠረት በፌደሬሽን የቆመች ኣገር ኣይደለችም። ተፈጥሮኣዊ ሂደትን ተከትላ የተመሠረተች ቀዳሚት ኣገር ናት። ይህም ኣገርን የመገንጠልና የመጠገን ፖለቲካዊ ስሜት የመስፋፋት ዕድል ስለሚከፍት ኤርትራ የራስዋ ሉዓላዊ ጥቅም ለማራመድ ስትል ለምሳሌ በኦሮሞና ሌሎች የመገንጠል እንቅስቃሴ እጅዋ የከተተች ስለሆነ የዚህ የመገንጠል እንቅስቃሴ የመብት ጥያቄ መንስኤና በእጅ ኣዙርም ኣጋዥ ሆና ልትቀጥልበት ትችላለች። ይህ ኣይነቱ የኮንፈደሬሽን ቅንብርም ኣገሪቱንም ወደ ባሰ የመነጣጠል ኣደጋ ሊያደርሳት ይችላል።

በሌላ ኣገላለፅ፣ ኤርትራ ሁለት እጆችዋ፣ ኣፍዋና ኣንድ እግርዋ ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ሁለተኛ እግርዋ ደግሞ እንደ ሉዓላዊት ኣገር ጥቅምዋን በምታደራጅበት ኣኳሃን ወደ ውስጥና ውጭ የመንቀሳቀስ መብት ይኖራታል። ከፈለገችም ዋና ስትራተጅያዊ መውጭ ካሰናዳች በኋላ ቀን ባመቸ ይህን ኮንፈደሬሽን ኣያስፈልገኝም የምትልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው።

ይህ በመነጋገር ላይ ያለነው የኮንፈደሬሽን ስርዓት እንግዲህ ዲሞክራስያዊ ባሕል ሥር ባልሰደደበት ሕብረተሰብ የመነጣጠል ፖለቲካ እንደ ራሱ የቻለ የመጨረሻ ዓላማ ተደርጎ በሚካሄድበት ኣገር ነው። ያለመተማመኑ ችግር ተስፋፅዮን መድሃንየ እንዳሉት ከኤርትራ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን እንድያውም በይበልጥ ከኢትዮጵያ ጭምር ነው። በእርግጥ ኤርትራ የነፃነት ጦርነት ከጀመረች ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንደታየው፣ የኤርትራ የፖለቲካ  ከበርቴዎች በኢትዮጵያ ጥላቻ ኣእምሮኣቸው የተመረዘ የኢትዮጵያን ህልውና ከሚፃረሩ የኣረብና ተመሳሳይ ኣገሮች ጥብቅ ግኑኝነት የመሠረቱ ናቸው። ይህን ያሳደጋቸው ባህልም በቀላሉ ማስጣል ያስቸግራል። የሻዕብያ ተቃዋሚ ተብለው በኣማራጭነት የሚቀርቡ ድርጅቶች እንኳ በኢትዮጵያ ያላቸው የጥላቻ ኣመለካከት ይብስ እንደሆነ እንጂ ኣይሻልም።

በነዚህ ከበርቴዎች ብቻ ተወስኖ ሳይቀር ማህበረሰቡ ራሱ ብዙ የስነልቦና ችግር ያለበትና በጎረቤቱ የትግራይ ሕዝብ ላይም የጥላቻ፣ ንቀት፣ ትዕቢት፣ ወዘተ ኣመሎች ያንሰራራበት መሆኑ ኣውስቻሎሁ። ይህም በሕዝቦች መሃከል ሰላም የነሳ ኣመኔታና በጎ ግኑኝነት ለማራመድ ዋና እንቅፋት ሆኖ የቆየ ትልቅ ችግር ነው። ይህ ራሱ ችላ መባል የሌለበት የግኑኝነቱ ወሳኝ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ በኮነፈደሬሽን ወይም ፌደሬሽን ለመቀላቀል በዲሞክራስያዊ ስርዓት ሕዝበ-ውሳኔ ወይም ሬፈረንደም የግድ ያስፈልጋል። ለምን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኣስከፊ ተመክሮው በመንግሥት ያለው እምነት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ። የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት ኣባላት የሆኑ ክፍለሃገራትም በጉዳዩ የግላቸው የመወሰን ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ በጥቅል የሚወሰን ሳይሆን በክፍለሃገር ደረጃ የትግራይ ሕዝብ ይህን የመቀላቀል ስምምነት ውድቅ ሊያደርገው ይችላል ማለት ነው።

### የፌደሬሽን ብቸኛ ኣማራጭነት

ኤርትራ ተመልሳ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን ለመወሃድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ ጥያቄ መሆን የለበትም። የተገነጠለችው የኤርትራ ህዝብ ጠቅላላ ጥያቄ መሆን

ይኖርበታል። ከላይ ከጠቀስኩዋቸው ምክንያቶች በመነሳት እንግዲህ ኤርትራ መዋሃድ የሚኖርባት ለኢትዮጵያ ልዩ ጥቅም ስለምታስገኝ ኣይደለም፤ የማህበረ-ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ተወግደው መቻቻል ከተፈጠረ፣ የኢኮኖሚው ሁኔታ ብቻ ብናጤን ጉዳቱ ያመዘነ ይሆናል። ኤርትራ ባላት የእድገት ፍላጎትና ግፊት ብዙ ወጭን የምትጠይቅ ትሆናለች። ለእድገት የሚያስፈልግ እጅግ ኣነስተኛ የኣገሪቱን ሃብት ትቀራመታለች ማለት ነው። ስለዚህ ለውህደቱ ኣንገብባቢነት በኣብላጫው መታየት ያለበት ኤርትራ ከምታስገኘው ጥቅም ኣኳያ ሳይሆን እንደ ማንም ፌደራላዊ ኣገሮች ወይም በበለጠ የሕዝቡ የታሪክ ኣንድነትና የባሕል ውህደት ለተቀላጠፈ የኣገሪቱን እድገት ስለሚረዳ በመገንዘብ መሆን ኣለበት። የኣካባቢውን ሰላም የነሳች ኤርትራ ቀጣይ ችግርም ማስወገድ ይቻላል።

ዳንኤል ክንዴ "... ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን ከሞላ ጎደል ታሪካቸው፣ ዘራቸው፣ ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸውና ባሕላቸው ኣንድ ዓይነት የሆነ ወይንም በጣም የተቀራረበ ነው ለማለት ይቻላል።" ሲሉ ገልፀውታል። "ከሞላው የጎደሉት" ኤርትራውያን ከየት የመጡ ናቸው? "ከሞላ ጎደል" ወይም "ለማለት ይቻላል" የሚሉት የጉድለት ኣገላለፆች ወደ ጎን እንተውና፣ ኤርትራውያን ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኤርትራውያን ይህን ቀላል ታሪክ ደጋግመው እንደገና መማር ያስፈልጋቸዋል። ኤርትራውያን የራሳቸውን ኣዲስ ማንነት በማነፅ ወደ ሌላው ህብረተሰብ ያስተጋቡት ኣስተሳሰብ ተከትለን "ናቸው ወይም ኣይደሉም" በማለት ቋንቋን በመሸራረፍ ጊዜ ማባከን ኣያስፈልግም።

ከሃዘሞ ተነስቶ ወሎ ድረስ ለግጦሽ የሚንቀሳቀስ የፕሮፌሰር ዳንኤል የበሬና ላም ወሬ ትተን ትክክለኛውን ታሪክ ብናወሳ የተሻለ ውጤት ኣለው። በጥቂቱ የጎንደር፣ የትግራይና ኤርትራ ትውልድ ብንመለከት የቀድሞ ሰፋሪ ኢትዮጵያውያን ወደ ደቡብና ሰሜን በየወቅቱ በመንቀሳቀስ ይፈልሱ እንደነበር ከኢትዮጵያ ሕዝብ የፍልሰት ታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል። እንግዲህ የሓማሴን (ሌላ ኣውራጃዎችም እንዲሁ) ትውልድ ብንመለከት ከሌላ ነገር ይልቅ ጎንደሬ መሆኑ በእርግጠኛነት ማስመስከር ይቻላል። ይህን ትውልድ ራሱ መተንተን ብችልም ኣልፈዋለሁ። ይህ በኤርትራውያን ትውልድ ቆጣሪዎች በደንብ የሚታወቅና የሚደጋገም ታሪክ ነው። ማረጋገጥ የምፈልገው ቁምነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደድንም ጠላንም ከሰሜን እስከደቡብ በትውልድ የተዋሃደ ኣንድ ሕዝብ መሆኑ ነው። ኣህጉር ዘሎ የመጣ ርዕዮተ-ዓለም በመዋስ ኣገሪቱን ከማወክ ይልቅ ታሪካዊ ኣንድነት ውህደቱን ለመጠበቅና ለማደስ መሠረታዊ መነሻ ምክንያት መሆን ኣለበት። ኤርትራም በዚህ የኣንድነት መንፈስ ነው ተመልሳ መቀላቀል ያለባት። ይህ የማንነት ጥያቄ ኤርትራውያን ራሳቸው ኢትዮጵያው ታሪካቸውና ማንነታቸውን መልሰው መገንዘብ ያለባቸው ጉዳይ ስለሆነ ለሚያደርጉት የውህደት ምርጫም በዚህ የሚወሰን ነው። ለዚህም ነው ለውህደት እንቅፋት የሆኑ ማህበራዊ የማንነት ቀውስ ችግሮች ራስን እያታለሉ መኖር ስለማይቻል ደጋግሜ መወገድ ኣለባቸው የምለው።

ለፀሃፊው መልእክት በዚህ መጠቀም ይቻላል- lgebre@live.ca